# <u>የገበያው ምሁር ዳግም ወጥ ረገጠ</u>

ደስታ አያሌው

መርካቶ ሰፈር ቅዳሜ ተሰዓት። አንኳን ሰዉ ውር ውር የሚሉትም ውሾች ሞቅ ያላቸው በሚመስልበት ጊዜ መቆም ያቃታችው ሰዎች ግድግዳ ተደግፈው አላፊ አግዳሚውን ሊስብኩ ሲሞክሩ ይታይ ነበር። የገበያ ምሁሮች  የምንላቸው ናቸው። የሚያውቁት ኢምንት ነው፤ ካለም በመጠጡ ፉዞ ሆኗል።  ራሱን ጌታቸው በጋሻው ፐብሊክ  ኢንቴሌክችዋል ብሎ የሚጠራው የቺካጎ ዘባራቂ የገበያ ምሁር ነው። የዞረበት፤ ነገር ባለሙ የጠፋው ግን ከሁሉም በላይ የሚጮህ !

ይህ ዘባራቂ ሰው ተሰዳብኩ ሲል ያማርራል-- ከነገሩማ ስድብ ሲያንሰው ነው። በሀገር ላይ ይጨማለቃልና። የጥፋት ጉዞ ኀደኛው ከማንም በፊት አንጎልህ በዚህ በዚያ ተሞልቷል ብሎ ሊወቅሰው የሚገባው እሱን ነበር። ጌታቸው ነኝ ባዩ የገብያ ምሁር ራሱን ከፖለቲካ መድረክ ማግለል  የነበረበት ድሮ ድሮ ነው። ጌታቸው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ቆየት ባለ መንገድ በአንድ ኣቅዋምና ድርጅት ጸንቶ መቆየት የማይችል በጥባጭ ነው። በቅርብ የሚያውቁት ይህ የገበያ ምሁር አንዲያው በአጭሩ በጥባጭ ቢባል ተገቢ ነው ይሉታል። ሌሎች ደግሞ ዶክተር ዜሮ፤ ኮሶ፤ በታኝና ሌላ ሌላም ብለው ይጠሩታል። "ሞት ለኢሕአፓ!” ብሎ ከዚያ ድርጅት ከተለየ በኋላ የቅርብ አጋሩ (ለትንሽ ጊዜ ያው አንደተለመደው) የሆነው ኣቶ መርሻ ወደ ድርጅቱ መልሶ መለመለው። ኢሕአፓ የተባለውም ድርጅት ከተመክሮ አልማር ብሎ አጥፊዎቹን ማቀፍ ልማዱ ነውና ይህን የገብያ ምሁር ማቀፍ ብቻ ሳይሆን ለአመራር ቦታም አበቃው። ሳይውል ሳያድር ከአቶ መርሻ ጋር ሆኖ ድርጅቱን ጥሎ ወጥቶ በድርጅቱ መሪዎች ላይ የክስና ውንጀላ ጅራፉን ማጮህ ጀመረ። አንደገና ሳይውል ሳያድር አቶ መርሻ ጋር ተጣላሁ ብሎ የብዙ ገጾች ውርጅብኝ አሰራጨባቸው። ዘመተባቸው። ከዚያም ትንሽ ጋብ አለና የግንቦት 7 ና በተለይም የኦነግ ዋና አፈ ቀላጤ ሆኖ አነሆ አየዘባረቀ ራሱን በማዋረድ ላይ ይገኛል። መካሪ ኀደኛ ቢኖረው ኖሮ ከፖለቲካውና ከመድረክ ርቆ--ሱባኤ አንኳን አይችልም፤ ንስሐም አይዋጥለትም – ዛሬ አሱ ሊምክረን አንደሚቃጣው አደብ አንዲገዛ በመከረው ነበር ።

የገበያው ምሁር ፎቅ ቤቱ ባዶና ውጥንቅጥ መሆኑ አየተረጋገጠ ነው። በቨርጂኒያ ከተማ በተካሄደው ስብሰባ ኀደኛው ሰዉን ሁሉ ሲስድብና ጀግኖችን ሲያንቋሽሽ የገበያው ምሁር ደግሞ ዕብሪት ባሳበጠው ጭንቅላቱ መላው የኦሮሞ ሕዝብ የኦነግ ደጋፊ ነው ብሎ ተጎነበሰ፤ ውዳሴ ሰጠ። በዚህም የተነሳ የገበያው ምሁር አሁንስ አበዛኸው ብለው ዜጎች ወቀሳ ቢያሰሙ ተሰዳብኩ በሚል ብሶበት በአንድነት ሀይሎች ላይ አነሆ ጸያፍ ጽሁፍ አሰራጭቷል። ዳግም ወጥ ረግጧል። ላሰማው አቅዋም ማጠየቂያው መሰረት ያለው ጥናት ሳይሆ አገሌን አግኝቸው ነገረኝ ዓይነት መደዴ መረጃ መሆኑ ይህን ምሁር በሉኝ ባይ ቀፎ ይበልጥ አዋርዶታል። ልማድ ሆኖብኝ ነው የቀባጠርኩት ብሎ ይቅርታ ከመጠየቅ ፈንታ (ማን ደፍሮት!) በዚህኛው ጽሁፉም ይህንኑ መሰረተ ቢስ ድምዳሜውን በ “ይመስለኛል”ና “አንድ ወዳጀ አንዳጫወተኝ” በሚል መልክ ሀገርን ያክል ክቡር ጉዳይ አቃሎ አቅርቦታል። “አብዛኛው ኦሮሞ ኦነግን ይደግፋል ብዬ አሁንም አምናለሁ” ሲልም ጽፏል።

ዘባራቂው ዶክተር የፈለገውን ማመን መብቱ ነው። ዜጎች ያከብሩኛል ብሎም ያምን የለ? አዋቂ ነኝ ብሎ ያምን የለ? ራሱን ቢያሞኝ ለእኛ የሚገደን ነገር የለም። ግን ይህን ዕምነቱን (ወይም ቅዠቱን) ሀቅ ነው ተቀበሉት ብሎ በተለይም መላውን የኦሮሞ ሕዝብና አልፎም ኢትዮጵያን ራሷን ለኦነግ ሊያስረክብ ሲነሳ ዝም ብሎ ማየት የሚቻል ኣይደለም። መላ የኦሮሞ ሕዝብ የኦነግ ደጋፊ አይደለም፤ ሊሆን የሚችልበትም ሁኔታ የለም። መላ የትግራይ ሕዝብ የወያኔ፤ መላ የኤርትራ ህዝብ የሻዕቢያ ደጋፊዎች አልነበሩም፤ አይደሉምም። ኦነግን ስናይ ደግሞ ቢያንስ ሁለት የኦነግ ቡድኖች አሉ። አስመራ የመሸገው የዳውድ ኢብሳ ቡድን ዛሬ ከበፊት በበለጠ ጠንካራ ሳይሆን ደክሟል። ማፈሪያው የገበያ ምሁር የአንድነት ሀይሎች ደቀዋል፤ "በቦታው የሉም" ወዘተ ብሎ ሲጽፍ ይህ የኦነግ ይዞታ ግን አይታየውም፤ ከታየውም ይክደዋል። ኦነግን ደግፉ ለማለትና፤ ለመለማመን የአንድነት ሀይሉን ማንኳሰሱን መርጧል። የጌታቸው ዋና ዓላማ የኣንድነት ሀይሎችን ማንቋሸሽና አነ ኦነግን ማደነቅ፣ ማሞገስ ነውና በአሳፋሪ ደረጃ (እሱ ግን ሀፍረትን ባያውቅም) ይዋሻል። የኦሮሞ ሕዝብ በአንድ ውሱን የፖለቲካ ቦይ የሚፈስ አይደለም። እንደማንኛውም ሕዝብ የሀሳብና የአቅዋም ልዩነት አለው። ከአንድነት ሀይሎች ጎን የቆመና የሚቆም አለ። ከወያኔ ጎን የሚሰለፍ አለ። ኦብኮና ሌሎች ድርጅቶችን (ኦህዴድን ጭምር) የሚደግፍ አለ ወዘተ.. ኦነግ ልክ እንደ ወያኔ ሁሉም ኦሮሞ ይደግፈኛል፤ ኦነግ ያልሆ አቅዋም ነው። ደንባራው ምሁር የኦነግ ጭፍን ኣባል ካልሆነ በስተቀር እዚህ ውስጥ ማን ከተተው? ማን ምስክር ሁን ለዚህ ቅጥፈት ብሎ አስገደደው?

በመጨረሻ ጽሁፉ ስህተቱን ከመድገሙ ሌላ ኢትዮጵያ መብታተን አለባት (ዘ ኤምፓየር መስት ቢ ዲስማንትልድ) ብሎ ኢብሳ ጉተማ የተባለው አዛውንት የጻፈውንም "ጠንቅቃችሁ ብታነቡት አንድ እንሁን ነው የሚለው" በሚል ሊያሞኝን ይሞክራል። ከገበያው ምሁር ውጪ እንግሊዝኛም ሆነ አማርኛ የሚያነብና የሚገባው የለም? ይህ በጣም ኣሳፋሪና ኣሳዝኝ ሸፍጥ ነው። ዕብሪትም ነው። የገበያው ምሁር ግን ተደናብሮ ማደናበር ነውና ተልዕኮው የጽሁፉ ርዕስ ራሱ የተሳሳተ ነው። ውዝግቡ የዚህን ሰው ዘባራቂ የዋሾ ምስክርነት የሚመለከት ሆኖ ሳለ ከኦነግና ሌሎችም አትነጋገሩ ያለ ሰው በሌለበት መነጋገር አስፈላጊነት በሚል ርዕስ ይችክችካል (የድህ መረቅ ስጋ ድንቹ ሲጠፋ ውሀው ይበዛል እንደሚባለው ሰውየው ብዙ ገጽ መጻፍን ያዘወትራል)። ንግግርን የከለከለ የለም – አይሆንም የተባለው ሀገርና ሕዝብን ለአንገንጣል ባዮች ማስረከቡ ነው።

ምሁር ተብዬው ዘባራቂ ጽሑፉን ሲጀምር ጀምሮ የጭቃ ጅራፉን የሚያጮኸው በአንድነት ሀይሎች ላይ ነው። ኢሕአፓን ይጠላልናም -- (ምክንያቱ ግልጽ ነው ደግመው ደጋግመው ሴራውን ውድቅ አድርገውበታልና፤ ይንቁታልና) በአሽሙር ያጠቃቸዋል። የአንድነት ሀይሎች መሪዎችን ግለኛና ቡድነኛ፤ የግል ጥቅም ፈላጊዎች፤ አዛውንቶች ወዘተ እያለ ይመታቸዋል (አዛውንት መሆን ሐጢያት ሆነ እንዴ?)። አንድ ብሔራዊ ድርጅት የማይቋቋመው በነሱ የተነሳም ነው ይላል። ህብረት ለመፍረሱም ምክንያቱን ድብቆ በነዚሁ በፈረደባቸው መሪዎች ላይ ይዘምታል። የዘር ድርጅቶችን አናቅርብ፤ ሕዝቡንም አናስረክባቸው ባለበት አፉ ደግሞ አትፍሩ ኤኤፍ ዲ ቁጥር ሁለት አይመሰረትም ብሎ ሊያዘናጋን ይሞክራል። ቁጥር አንድን ተቃውሚ ነበርና ለእኔ ተውትም ባይ ነው! ለገበያው ምሁር የአንድነት ሀይሎች መድረክና ኢዴፓህ ብቻ ናቸው። ህብረት

ሲል ግን የዶክተር በየነን ይሁን የመቶ አለቃ ኣያልሰውን አይገልጽም። ለሰጎኑ ምሁር ሌሎች ድርጅቶች የሉም፣ ከዘር ድርጅቶች ውጪ! ወያኔያዊ ፈሊጥ! ያለን ነገር የለም ማለት!

ከሁሉም በላይ በጣም ጸያፍ የሆነው የዚህ ዘባራቂ ሰው ጽሁፍ የኢትዮጵያን ህልውና የሚመለከት ነው። በግለሰብ አጅ አጅ ጨዋታ አጅቦ የሀገራችንን ህልውና አቅልሎ በማቅረብ መቀለጃ አድርጎታል። "<u>በወያኔ ትንሽ የብዕር ጭረት የኢትዮጵያ ህልውና ትጠፋለች</u> " ሲል ይህ መሃይም ሳያፍር ጽፏል። ይህ ምን ይባላል? ሕዝብን መናቅና ለወያኔ መስገድ አይደለምን? እንዲህ ቀሎ ያለን ህልውና ለመታደግና ለማዳን ከኦነግ አብሩ፤ ኦነግና መሰሎቹን ተጠጉ ወዘተ ብሎ ለመማጸን ነው ያያ ኮሶ ምክር። በርግጥም የሰውየው ጽሁፍ ርስበርሱ የተቃረነ ነው። ሌላ ምን ጠብቀን? ይህ ሰው <u>"በኦነግ ውስጥ የሚያበረታቱ ለውጦች ይታዩኛል</u>" ሲልም ጽፏል። ሰውየው ይቅማል? ያቺን መጥፎ ዕጽ ያቦናል? የሚል ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው። ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው እንዲሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኦነጎች <u>አቅዋማችን ምንም አልተቀየረም</u> እያሉ እስካሁን ድርቅ ብለው አሉና ዶክተሩ የሚያየው ራዕይ ከየት የመጣ ነው? ከመዋሸት ሌላስ ምን ሊባል ይቻላል? አቅዋም ከቀየሩስ ለምን ለገበያው ምሁር ብቻ የሚታይ የሚገለጥ ሆነ? የአመራራቸው አባል ነው?

ሌላ ጌታቸው ኮሶ የተያያዘው ጨኸት (በተለይ በጣም የሚጠላቸውን የተወሰኑ የድርጅት መሪዎችን የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው) የድርጅቶች መሪዎች (የአንድነት ሀይሎችን እንጂ እነ ዳውድን ወይም የኦብነጉን የዚያድ ባሬ መሪ ጀኔራል አይመለከትም) አርጅተዋል፤ ለለውጥ እንቅፋት ሆነዋል የሚል ነው። ይህን በንጽጽር ለማስረዳት የገበያው ምሁር ግንቦት 7 መሪዎቹ ወጣቶች መሆናቸውን፤ የፈረደባት ብርቱካን ወጣት መሆኗን፤ ሌሎች ወጣት ተብዬዎችም በዚህም በዚያም መኖራቸውን ይጠቅሳል። ከነዚህ አንዱ የአመጽ ቀነ ቀጥሮ የሰጠና የተቃዋሚ ሀይሎችን መሳቂያ መሳለቂያ ሊያደርግ የቃጣ "ብልህ" ሰው መሆኑን ጠቅሰን እንለፍ ። ወጣት ሲልም ለገበያ ምሁሮች የአሳት አሎሎ የሆኑትን ወክንዶችና ታጋይ ሴቶችንም መጥቀሱ ያቅተዋል። የተጠቀሱት ወጣት ተብዬዎቹ አውን የፖለቲካ ብስለት አላቸው የላቸውም የሚለውን ለጊዜው እንለፈውና ለመሆኑ ወጣት የሚለው ዕድሜ ክልሉ የት ላይ መሆኑን ምነዋ አዛውንቱ ጌታቸው ሳይጠቅስልን ቀረ? ተመክሮ ያካበቱ መሪዎችን ማጥቃቱ የተጧጧፈው የአንድነት ሀይሎችን መሪና ዕውቀት ለማሳጣት መሆኑ የታውቀና የተጋለጠም ነው። በትግል ጽንቶ መቆየት ራሱም ጥፋት ተብሎ ሊፈረጅ ጫጫታ አይደለም እንዴ? አፍራሹ ጌታቸው የሚሰድባቸው በጽናት በትግል የቆዩ የድርጅቶች መሪዎች ጥፋታቸው አዛውንት መሆናቸው ሳይሆን ለከሀዲዎችና አድር ባዮች በፍጹም አልመች በማለታቸው፤ በሀገር ህልውና ላይ እንደራደርም፤ ለገንጣይ አጅ አንሰጥም በማለታቸው መሆኑ የሚታውቅ ነው። የኦነጉን ከበሮ ያበሳጨው ይህ ነው። በወጣትነት ከሆነማ መለስም ወጣት ነበር፤ ልደቱም ወጣት ነው፤ ድርጅት ሊበትን ሲነሳና ሲክድ አንድ ጌታቸው የሚባል የጥፋት ቋትም ወጣት ነበር ።

ዜጎች፤ ተባብረን ይህን የገንጣዮች መጋዣ ወደ ፖለቲካ ምድረበዳ እንሰደደው።